# በምርምር ጥናት ውስጥ ያሉዎት መብቶች፡- በግዳጅ ፍልሰት ጉዳይ ላይ በሚደረግ ማንኛውም የምርምር ጥናት ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች የሚሆን የመረጃ ሉህ

በምርምር ፕሮጀክት ውስጥ መሳተፍዎ ድምጽዎ እንዲሰማ ለማድረግ ዕድል ይሰጥዎታል፣ ነገር ግን የማያመች፣ ጊዜን ወይም ገንዘብን የሚጠይቅ፣ እንዲሁም/ወይም የአካል ወይም የስሜት ምቾት እንዳይኖርዎት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህም የመረጃ ሉህ ቁልፍ የሆኑ ቃላቶችን በዝርዝር ይገልጻል፣ እንዲሁም መብቶችዎን ይዘረዝራል፡፡



**በፈቃደኝነት፣ በመረጃ የተደገፈ ስምምነት**

ይህ ማለት በሚደረገው የምርምር ፕሮጀክት ውስጥ ለመሳተፍም ሆነ ላለመሳተፍ ከፈለጉ እርስዎ ብቻ መወሰን ይችላሉ ማለት ነው፣ ይህንንም እስቲ ከፋፍለን ከዚህ በታች እንየው፡-

*ፈቃደኛ መሆን ማለት በራስዎ ነጻ ፈቃድ መወሰን ይችላሉ ማለት ነው* —ነገር ግን ለመሳተፍ ፈቃደኛ ባይሆኑም እንኳ ፈቃደኛ ባለመሆንዎ ምክንያት የሚከተል ምንም ዓይነት ቅጣት አይደርስዎትም፣ እንዲሁም በዚህ ለመሳተፍ በመስማማትዎ ምክንያት የሚያገኙት ዋና ጥቅማ-ጥቅም (ጠርቀም ያለ ገንዘብ መጠን ዓይነት) ምንም አይኖርም፣

- ለመሳተፍ ፈቃደኛ ባለመሆንዎ ምክንያት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ሊከለከሉ አይችሉም፡፡
- አንድ ግለ ሰብ፣ የመንግሥት ባለሥልጣን፣ ወይም ድርጅት መሳተፍ እንዳለብዎት ቢወተውትዎት እንኳ እርስዎ ግን ይህን ለማድረግ ግዴታ አይኖርብዎትም፡፡ እርስዎ ምንም ባይሳተፉም እንኳ፣ አሁንም ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ወይም የገቢ ምንጮችን የማግኘት መብትዎ የተጠበቀ ነው፡፡

***ያወቁ መሆን ማለት የሚካሄደው ምርምር ስለምን እንደሆነ፣ ምን ሊያደርጉ እንደሚጠየቁ፣ ቢሳተፉ ደግሞ ምን ዓይነት ጥቅሞችና ጉዳቶች እንዳሉበት የማወቅ መብት አለዎት ማለት ነው፡፡***

- ጥናቱ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እና በትክክል ከእርስዎ ዘንድ ምን እንደሚፈለግ መጠየቅ አለብዎት፣
- ጥናቱ እንዴት ለሌሎች ሊጋራ እንደሚችል፣ እንዲሁም የምርምር ውጤዎችን እንዴት ማገኘት እንደሚችሉ የማወቅ መብት አለዎት፣

© Christina Clark-Kazak, 2021. Translation by Access Alliance Language Services. CC BY-NC-SA 4.0.

- ይህንንም መረጃ እርስዎ በሚረዱት ቋንቋ የማግኘት መብት አለዎት፣ የቋንቋ ትርጉም ወይም ማስተርጎም የሚያስፈልግዎት ከሆነ መጠየቅ ይችላሉ፡፡
- ጥያቄዎች ወይም ሥጋቶች ካሉዎት ደግሞ ደውለው ሊያናግሩ የሚችሉበትን የግኑኝነት መረጃ ተመራማሪው ለእርስዎ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሚደረገው ጥናት ለመውጣት ከፈለጉ፣ ይህን የግኑኝነት መረጃ መጠቀም ይቻላል፡፡
- በማንኛውም ጊዜ ጥያቄዎችን የመጠየቅ መብት አለዎት፣

**ስምምነት ማድረግ ማለት እርስዎ እንዲሳተፉ በግልጽ ተስማምተዋል ማለት ነው፡፡**

- እርስዎን ወክሎ ሊስማማ የሚችል ማንም አይኖርም (ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ወይም ውስን የግንዛቤ ችሎታ ካላቸው በስተቀር፣ (በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ስለሚኖረው የሙብት መረጃ የሚከተሉትን ይመልከቱ)፣
- በአብዛኛው ጊዜ በምርምር ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆንዎን በይፋ ለማሳየት አንድ ቅጽ እንዲፈርሙ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ ቅጹን በተመለከተ ደግሞ ለመፈረም ወይም ላለመፈረም ከመወሰንዎ በፊት ከዘመዶች፣ ከጓደኞች፣ ከሠፈራ ሠራተኞች፣ ከማኅበረሰብ አባላት እና ወይም ከማንኛውም ሰው ጋር የመመካከር መብት አለዎት፡፡ ተመራማሪውም እርስዎ የፈረሙበትን የቅጽ ቅጂ ለእርስዎ መስጠት ይኖርበታል፡፡
- በተመራማሪው የምርምር ሥነ-ምግባር ቦርድ (REB)[1] መስፈርቶች ላይ በመመርኮዝ፣ ይህ ሁልጊዜ የሚቻል ባይሆንም እንኳ፣ እርስዎ ከፈለጉ በዚህ አሠራር ምትክ ስምምነትዎን በቃል ለመስጠት መጠየቅ ይችላሉ፡፡
- በማናቸውም ጊዜም ከምርምር መውጣት ይችላሉ—የምርምር ጥናቱንም የማጠናቀቅ ግዴታ የለብዎትም፡፡ ለማቋረጥ ከወሰኑ፣ ማንኛውም የእርስዎ መረጃ ጥቅም ላይ እንዳይውል የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡
- እንዲሁም ማንኛውም ለየት ያለ ጥያቄ ላለመመለስ ወይም በማንኛውም የምርምር ገጽታ ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆን ይችላሉ፡፡

[1] የምርምር ጥናት ሥነ-ምግባር ቦርድ (REB) ማለት ተመራማሪው በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን የሥነ ምግባር መርሆዎች እንደሚገባ መከተሉን ለማረጋገጥ፣ የምርምር ፕሮጀክቶችንም የመገምገም ኃላፊነት ያለበት በተመራማሪዎች ተቋም ውስጥ የሚገኝ ኮሚቴ ነው፡፡ የምርምር ጥናት ሥነ-ምግባር ቦርድ (REB) ስለ ምርምሩ ጥናት ያሉዎትን መብቶች ለማስተዋወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

© Christina Clark-Kazak, 2021. Translation by Access Alliance Language Services. CC BY-NC-SA 4.0.

**በምርምር ጥናት ውስጥ ያሉዎት መብቶች፡- በግዳጅ ፍልሰት ጉዳይ ላይ በሚደረግ ማንኛውም የምርምር ጥናት ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች የሚሆን የመረጃ ሉህ**

*ፈቃደኛ መሆን ማለት ለአካለ መጠን ከደረሱት የብዙዎች ዕድሜ ክልል በታች የሆነ ሰው ወይም ውሱን የግንዛቤ ችሎታ ያለው ማንኛውም ሰው ለመሳተፍ ሲስማማ ማለት ነው፡፡ ጉዳዩ ይኸ ዓይነተ የሚሆን ከሆነ ደግሞ፣ ጥናቱ እንዲቀጥል ለማድረግ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ፈቃድ ወይም ስምምነቱን መስጠት ይኖርበታል፡፡*



*የግል ማንነትዎንና እና በምስጢር የሚታቀብ የግል ጉዳይዎ የተጠበቀ እንዲሆን መብትዎ ነው፣ ማለትም አንድ ተመራማሪ ያለ እርስዎ ግልጽ ፈቃድ በምርምር ጊዜ ውስጥ የእርስዎን ማንነት ሆነ በምርምሩ ጊዜ የሰጧቸውን መልሶች መለየት አይችልም ማለት ነው፤ ሊታሰቡባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮችም አሉ፡-*

**የግል ማንነት ጥበቃ ማለት ከጥሰት ወይም ከጣልቃ ገብነት ነጻ የመሆን፣ እንዲሁም ስለ እርስዎ ያለውን ማንኛውም ዓይነት መረጃ መቆጣጠር መቻል ማለት ነው፡፡**

- ይህም በጥናቱ ጊዜ እርስዎ እንደ ተሳተፉ በማይታወቅበትም ሆነ እርስዎን የሚያውቁ ሁሉ ሊለይዎት በማይችሉበት የግል እና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ላይ ምርምሩ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት አለዎት፣
- በምርምር ውጤዎች ውስጥ በግል እንዲታወቁ መፈለግዎንና አለመፈለግዎን የመምረጥ መብት አለዎት፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ግን ተመራማሪው ትክክለኛ ስምዎን መጠቀም ላይችል ይችላል፣ ምክንያቱም እርስዎ ስምዎ እንዲታወቅ በግልጽ ቢጠይቁ እንኳ የእርስዎ መታወቅ ደግሞ በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉትንና እንዲታወቁ የማይፈልጉትን ሌሎች ሰዎች ሊያጋልጥ ስለሚችል ነው፡፡
- ከምርምር ጥናቱ የተገኘው መረጃም እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል የማወቅ መብት አለዎት፡፡
- ተመራማሪዎችም ቢሆኑ የጥናቱ ግኝቶችን አስመልክተው እርስዎ እንዴት ማወቅ እንደሚችሉ በግልጽ ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

**በምስጢራዊነት ማቀብ የግል መረጃ ጥበቃ ነው፡፡**

- ተመራማሪው የተሰበሰበውን መረጃ በሌሎች ሰዎች ተደራሽ በማይሆንበት መንገድ እንዲቀመጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፣
- መረጃዎ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚከማችና ለማን ተደራሽ መሆን እንደሚችል የማወቅ መብት አለዎት፡፡
- ተመራማሪውም ይህንን መረጃ ለሌላ ሦስተኛ አካል መስጠት ወይም መሸጥ አይፈቀድለትም፡፡

© Christina Clark-Kazak, 2021. Translation by Access Alliance Language Services. CC BY-NC-SA 4.0.

**በምርምር ጥናት ውስጥ ያሉዎት መብቶች፡- በግዳጅ ፍልሰት ጉዳይ ላይ በሚደረግ ማንኛውም የምርምር ጥናት ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች የሚሆን የመረጃ ሉህ**

- በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት፣ ጉዳይ በራስዎ ላይ ጉዳት የሚያመጣ፣ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ካገኘው፣ ተመራማሪው መረጃውን ለሌሎች የማሳወቅ ሥነ-ምግባራዊ ግዴታ ሊኖረው ይችላል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉት በምስጢር የማቀብ ገደቦች የስምምነት ቅጹ ላይ በግልጽ መታየት አለባቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጠራጠሩ ከሆነ ይጠይቁ! እንዲሁም ስለ እርስዎ የሚሰበሰቡት የማናቸውም መረጃዎች የሰዎች ማንነት እንዳይገልጡ ለማድረግ (ከዚህ በታች ያለውን ይመልከቱ) በጽኑ የመጠየቅና የማሳሰብ መብት አለዎት፡፡
- ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት፣ የጥናት ተመራማሪው ከወንጀል ድርጊት ጋር ንኪኪ ያለው ሆኖ ካጋጠመው ለፖሊስ የማሳወቅ ግዴታ ሊኖረው ይችላል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉት በምስጢር የማቀብ ገደቦች የስምምነት ቅጹ ላይ በግልጽ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጠራጠሩ ከሆነ ይጠይቁ! እንዲሁም ስለ እርስዎ የሚሰበሰቡት የማናቸውም መረጃዎች ማንነትዎ እንዳይገለጥ ለማድረግ በጽኑ የመጠየቅና የማሳሰብ መብት አለዎት፡፡
- በኢንተርኔት መስመር ላይ ለሚደረጉ ማንኛውም የዳሰሳ ጥናቶች ምላሽ ለመስጠት፣ እንደ አሜሪካ በመሳሰሉ አንዳንድ አገሮች ውስጥ የሚገኙ ለሌሎች ኮምፒተሮች (servers) መረጃን በሚበትኑ ወይም መረጃን በሚቆጣጠሩ የተከማቸ ማንኛውም መረጃ በመንግሥት ተደራሽነት ሊኖረው እንደሚችል ማወቅ ይኖርብዎታል፡፡ ይሁን እንጂ ተመራማሪው እንደዚሁ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ግላዊ ማንነትና ምስጢራዊነትን እንዴት ሊጠብቅ የሚችልበትን ዋስትና መስጠቱን ለማረጋገጥ የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡

**ማንነትን መደበቅ ማለት መረጃው ሊታወቅ የሚችልበት ምንም ዓይነት ሁኔታ የለም ማለት ነው፣ ስለዚህም የተወሰኑ የምርምር ግኝቶቹ በክትትል ወደ ማንኛውም ግለ ሰብ መመለስ አይቻልም ማለት ነው፡፡**

- ይህ ደግሞ ከላይ ለተብራራው ምስጢርን የማቀብ ገደቦች አንዱ መፍትሄ ይሆናል ማለት ነው፡- በዚህም መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ማንም—ተመራማሪው ራሱ እንኳ ሳይቀር—ከዚህ መረጃ ጋር የተያያዘ ሰው ማን እንደሆነ ማወቅ የማይችልበት አሠራር እንደሆነ የሚያረጋግጥ ሂደት ነው፡፡.
- የእርስዎ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ሁኔታ እስከ አሁን ድረስ መደበኛ እልባት ያላገኘ ከሆነ፣ ተመራማሪዎች የማንነትዎን መረጃ በሚስጢር ሊጠበቅ እንደሚችልና እንዳይገለጽ ለማድረግ እንዴት ዋስትና ሊሰጡዎት እንደሚችሉ መጠየቅ አለብዎት፡፡ አለበለዚያ ግን የምርምር ግኝቶች ውጤቶች እርስዎን አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ፡፡

© Christina Clark-Kazak, 2021. Translation by Access Alliance Language Services. CC BY-NC-SA 4.0. 

**በምርምር ጥናት ውስጥ ያሉዎት መብቶች፡- በግዳጅ ፍልሰት ጉዳይ ላይ በሚደረግ ማንኛውም የምርምር ጥናት ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች የሚሆን የመረጃ ሉህ**



**ምንም ዓይነት አደጋ አለማድረስ የሚለው መርሆ የተመራማሪው ግዴታ ነው ሲባል፣ የእርስዎ ምቾት፣ ክብር እና ደኅንነት መጠበቅ ሁል ጊዜ ግምት ውስጥ መግባት አለበት ማለት ነው፡፡**

- በሚደረገው የምርምር ሂደት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ምቾትዎ የማይጠበቅ ሆኖ የሚሰማዎት ከሆነ ግን፣ ተመራማሪውን የማነጋገር ወይም የማሳወቅ መብት አለዎት፡፡
- እዚህ ላይ ተመራማሪው ምቾት እንዳይሰማዎት ማድረጉን የሚቀጥል ከሆነ ግን፣ እርስዎ በጣም ለሚያምኑት ሰው (ለጓደኛ፣ የቤተ ሰብ አባል፣ የሠፈራ ጉዳይ ሠራተኛ፣ የማኅበረሰብ አባል) የግድ መናገር ይኖርብዎታል፣ እንዲሁም የተመራማሪውን የምርምር ጥናት ሥነ-ምግባር ቦርድ (REB) ማነጋገር ይኖርብዎታል፡፡ ይህም የግኑኝነት መስመር መረጃ በስምምነት ቅጹ ላይ መታየት አለበት ወይም እርስዎ በኢንተርኔት ላይ መረጃውን ማፈላለግ ይችላሉ፡፡ ሁሉም ዩኒቨርስቲዎች እና ሆስፒታሎችም የምርምር ጥናት ሥነ-ምግባር ቦርድ (REB) ወይም ተመሳሳይ ኮሚቴ አላቸው፡፡
- የእርስዎን የባህል፣ የሃይማኖትና የጎሳ ታሪክዊ ዘይቤ በሚያስከብር መልኩ በአክብሮት የመስተናገድ መብት አለዎት፡፡

© Christina Clark-Kazak, 2021. Translation by Access Alliance Language Services. CC BY-NC-SA 4.0.



CENTRE FOR REFUGEE STUDIES
CANADIAN COUNCIL FOR REFUGEES
CONSEIL CANADIEN POUR LES RÉFUGIÉS
CARFMS/ACERMF